INQUEST

TRUTH, JUSTICE AND ACCOUNTABILITY

# በግሪንፌል ታወር የእሳት አደጋ ቤተሰቦቻቸውን ላጡ መረጃ

ከ 35 አመት በላይ ኢንክዌስት ሞትን በተመለከተ ምስጥራዊነቱ የተጠበቀ ምክር ሲሰጥ ቆይቷል እንዲሁም ምርራቸውም የተገደሉ ሰዎች፣ የማህበረሰብ ቡድን፣ ጠበቆችና የበጎ ፈቃደኝነት ዘርፍ ነው፡፡ እኛ ከመንግስት ነጻ ነን፡፡ ይህ ማለት በልዩ ሁኔታ በግሪንፌል ታወር ላይ በደረሰው የእሳት አደጋ የተለያዩ አይነት ምርመራዎችን ምክር እንለግሳለን፡፡

በህግ አካሄዱ እውነት እንዲወጣ፣ ፍትህ እንዲገኝና ሀላፊነት የሚወስደው አካልም ተጠያቂ እንዲሆን እንሰራለን፡፡

ይህ በራሪ ወረቀት ከቤተሰቦች የምንጠየቀውን የተወሰኑ አስቸኳይ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ እንዲሁም መብቶትን ለማስጠበቅ የህግ ምክርን **ልዩ ሙያ ካላቸው ጠበቃዎት በቻሉት ፍጥነት ያግኙ፡፡** ከኢንክዌስት ቡድኑ ትክክለኛውን ጠበቃ እንዲያገኙ ልናግዞት እንችላለን፡፡ ለዚህና ለሌላ ምክር፣ ኢንክዌስትን በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ፡-


**ስልክ: 020 7263 1111**

ኢሜል: inquest@inquest.org.uk

ድረገጽ: www.inquest.org.uk


እባክዎን ያስታውሱ በሌሎች ጥሪዎች ስራ ከበዛብን፣ መልሶችን የሚያስተናግድ የማሽን አገልግሎት የምንጠቀም ሲሆን መልእክትዎን ከተዉልን መልሰን ልንደውልሎት እንችላለን፡፡

ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ በኢንክዌስት መመሪያ መጸሀፋችን ላይ ይገኛል፡፡ በኢንተርኔት ማሰሻዎት ላይ የሚከተለውን የድረገጽ አድራሻ ይጻፉለ፡- bit.ly/InquestHandbook

**የወንጀል ምርመራ ይደረጋል?**

የሜትሮፖሊታን ፖሊስ በአደጋው ላይ የወንጀል ምርመራ እያካሄደ ነው፡፡ የፖሊስ ምርመራውን ለማጠናቀቅ የተወሰኑ ወራት ሊወስድ ይችላል፡፡ ይህን የወንጀል አደጋ እንዲከሰት ያደረው ግለሰብ ወይም ድርጅት በክራውን የእህግ አገልግሎት አማካኝነት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

**ፖሊስ የነፍስ ግድያ ክስን ይመለከታል?**

ጥፋቱ በቸልታ የደረሰ ነፍስ ግድያን ወይም ተባባሪ ነፍስ ግድያን ከግምት ያስገባል፡፡ ፖሊስ/ሲፒኤስ በቂ መረጃ አለ ብለው ካመኑ፣ ክሱ በተለመደው መንገድ ይካሄዳል፡፡ በቂ መረጃ የለም ብለው ካመኑ፣ ተጎጂዎች ውሳኔውን እንደገና የመመልከት መብት አላቸው፡፡

**የህዝብ ጥያቄ ይኖራል?**

መንግስት ሙሉ ለሙሉ የህዝብ ጥያቄን ያሳውቃል፡፡ ተጎጂዎችና ከአደጋ ተራፊዎች በሚፈልጉት ሁሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የህግ ውክልና ክፍያን ያገኛሉ፡፡

ጥያቄው በቃለመህላ ያለ ማስረጃን ያዳምጣል እንዲሁም ተሳታፊዎች ማስረጃው ላይ ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ይህም ጊዜአዊ ግኝቶችን የሚያስገኝ ሆኖ ከሌሎች ነገሮች ጋር ተመሳሳይ የግንባታ ችግር በሚታይባቸው ሌሎች ህንጻዎች ላይ ያሉ ነዋሪዎችን በፍጠነት ጥበቃ ለማድረግ ያስችላል፡፡

ለመሳተፍ የሚፈልግ ካለ ለ ‹‹ዋና ተሳታፊዎች›› ማመልከት ይችላል፡፡ ይህ በጉዳዩ ላይ ‹‹በቀጥተኛና ወሳኝ ሚና›› የሚጫወቱ ወይም ሊጫወቱ የሚችሉ እንዲሁም ‹‹ጉልህ ፍላጎት›› ያላቸውን ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡

ዋና ተሳታፊዎች ምስክሮች ማንኛውንም አይነት ጥያቄ ሊጠይቁ፣ በምርመራው ላይ የመክፈቻና የመዝጊያ መግለጫን መስጠት እንዲሁም የጥያቄውን ሪፖርት ቅጂ መቀበል ይችላሉ፡፡

**ምርመራው ነጻ ነው?**

ለተጎዱት አካላት ጠንካራ የህግ ውክልና እንደሚኖር፣ ምርመራው ነጻ በመሆንና ወሳን ግኝቶችን ከማግኘት አንጻር የተጎጂዎችንና ከአደጋ የተረፉትን ፍላጎት የሚያሟላ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ቀደም ብለው የህግ ውክልናን በፈለጉ ቁጥር ድምጾት የበለጠ ሊሰማ ይችላል፡፡

ሙሉውን የይፋዊ ምርመራ መግለጫችንን ለመመልከት፣ የሚከተለውን አድራሻ በድረገጽ ማሰሻዎት ላይ ያድርጉ፡- bit.ly/GrenfellInquiry

**ኢንክዌስት ምንድነው?**

ኢንክዌስት ማለት ሰውየው ማን እንደሆነና የት፣ መቼና እንዴት እንደሞተ እውነታው እንዲወጣ ምርመራ የሚያደርግ ማለት ነው፡፡ በመርማሪው፣ አንዳንዴም በዳኞች የሚደረግ ህጋዊ አካሄድ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ዋና መርማሪዋ ኤችኤም ዶ/ር ፊዮና ዊልኮክስ ከማእከላዊ ምእራብ ለንደን መርማሪዎች ፍርድቤት ናቸው፡፡ መርማሪዋ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊከሰት የሚችሉ የህይወት ህልፈቶችን ከግምት በማስገባትና መለወጥ የሚገባቸው ነገሮች ላይ ምክርን ይሰጣሉ፡፡ ችሎቱ የሚሰማው በፍርድ ቤት ሲሆን ቤተሰቦችም መወከል ይችላሉ፡፡

**ኢንክዌስት የሚደረገው መቼ ነው?**

አስከሬኑ እንደተገኘና እንደተለየ በተቻለ ፍጥነት መርማሪው ምርመራውን ይከፍታል፡፡ ይህም በችሎት በአጭሩ የሟቹ ስም፣ እድሜና በጣም ዝርዝር ነገሮቹና ለሞቱ ዋና ምክንያት የሆነው ነገር ለፍርድ ቤቱ በግልጽ ይነገራል፡፡ በተመሳሳይ ግዜ ብዙ ጥያቄዎች በተመሳሳይ ግዜ ሊከፈቱ ይችላሉ፡፡ መርማሪውም የወንጀል ምርመራውን ያዘገየውና የህዝብ ጥያቄ ሊኖር ይችላል፣ ይህም መሆን ያለበት መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

አንዴ የወንጀል ምርመራውና ጥያቄው እንዳበቃ መርማሪው ጥያቄዎቹ አስፈላጊ እንደሆኑና እንዲቀጥሉ ይቻል እንደሆን ይወስናል፡፡

**የጠፋ ሰው እንዳለ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?**
ስለ ጠፉ ዘመዶች ጥያቄ የሚቀርበው በምእራብ ለንደን በሚገኘው በዌስትዌይ ስፖርትስ ማእከል **ለሜትሮፖሊታን ፖሊስ ተጎዎች ቢሮ** በአካል በመገኘት ወይም በ **0800 0961 233** ላይ ለተጎጂዎች ቢሮ በመደወል ይሆናል፡፡

የጠፋ ሰው እንዳለ ሪፖርት አድርገው እንደገና የተገናኙ እንደሆነ ለተጎጂዎች ቢሮ ማሳወቅ ይኖርቦታል፡፡

መርማሪው በግሪንፊል ታወር ስለደረሱት የሕይወት መጥፋቶች በሙሉ ያውቃል፡፡ መለየቱ ከዘመድ ጋር በመሆን ከቤተሰቡ ጋር ግንኙነት ከሚያደርግ ባልደረባ ጋር ይከናወናል፡፡ የጠፋ ሰው እንዳለ ሪፖርት ካደረጉ በኋላ የተገኘ ነገር ከሌለ የሞቱትን ማንሳትና መለየት አስቸጋሪ ስለሆነ ሊሆን ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ቀንም ለቤተሰቦቻቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ እንደሚያልፍ እንረዳለን፡፡ ኢንክዌስት ከመርማሪ ፍርድቤትና የተጎጂዎች ቢሮ ጋር በመገናኘት በዚህ ላይ እገዛ ያደርግሎታል፡፡

**ለዘመዶቼ አስክሬን ሀላፊነቱን ማን ይወስዳል?** የተለያዩ ምርመራዎች በሚደረጉ ግዜ፣ መርማሪው አስክሬኑን ይቆጣጠራል፣ ከሱ ፈቃድ ውጪም ለቀብር አይሰጥም፡፡

አስክሬኑ እንዲለቀቅ የሚቀርብ ጥያቄና ከቀብር በኋላ ያለው ነገር ለመርማሪው ቢሮ ይቀርባል፡፡ ቁጥሩ **020 7802 4750** ነው፣ ነገር ግን ጥያቄው መቅረብ ያለበት በቀጥታ ከላይ ላለው የጉዳተኞች ቢሮ ነው፡፡

**እየተካሄደ ያለውን የአስክሬን ምርመራ ማስቆም እችላለሁ?**
በአጠቃላይ የአስክሬን ምርመራው በጣም በፍጥነት የሚካሄድ ነው፡፡ የአስክሬን ምርመራውን የሚቃወሙ ከሆነ በአፋጣኝ ለመርማሪው ያሳውቁ ይህም ሌሎች አማራጮችን ከግምት ለማስገባት ይጠቅማል፡፡ መርማሪው የአስክሬን ምርመራው አስፈላጊ እንዳልሆነ ከወሰነ ያለጥያቄ እንዲወሰድ ልትፈቅድ ትችላለች፡፡

**አስክሬኑን መመልከት እችላለሁ?**
በአጠቃላይ፣ አዎ ይህም በመርማሪው ቢሮ በኩል የሚመቻች ይሆናል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ለአብነትም በጣም የተጎዳ ቁስል ካለ፣ መርማሪው አስክሬኑን እንዳይመለከቱ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል ወይም ለተወሰነ ግዜ ብቻ የሚመለከቱት ይሆናል (ለምሳሌ በመስተዋት ተሸፍኖ)፡፡ ምክሩን መቀበል የእርሶ ፋንታ ይሆናል፡፡ የዘመዶትን አስክሬን እንዳይመለከቱ የተከለከሉ መስሎ ከተሰማዎት የህግ ድጋፍ መሻት ይችላሉ፡፡

**አስክሬኑን የሚለየው ማነው?**
የቤተሰብ አባል ወይም የቅርብ ጓደኛ በመመልከት አስክሬኑን መለየት ይችላል ነገር ግን ያ የማይቻል ከሆነ ሌሎች መንገዶች ማለትም እንደ አሻራ መውሰድ ወይም የጥርስ ምርመራ በማድረግ ወይም የዲኤንኤ ናሙና መውሰድ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

**መርማሪው የተለያዩ የባህልና እምነቶች እንዲሁም ከህልፈት ጋር የተገናኙ ልምዶችን ከግምት ያስገባል?** ስለ እምነቶትና ልማዶችዎት ለመርማሪው ማሳወቁ ጠቃሚ ይሆናል ይህም በህግ ማእቀፍ ስር ሆኖ በፍላጎቶችዎት ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ያደርገዋል፡፡

**የቀብር ስነስርአቱን ማድረግ የምችለው መቼ ነው?**
መርማሪው አስክሬኑን ፈቅዶ እስካለቀቀ ድረስ ቀብሩ መካሄድ አይችልም ነገር ግን ምርጫዎት የሆነውን የቀብር ስነስርአት ዳይሬክተሩን ቀድሞ ማግኘት ለዝግጅቱ ሊያግዞት ይችላል፡፡ ምን አልባት ወጪዎትን የሚያወራርዱ ከሆነ ደረሰኞቹን ማስቀመጥ ይኖርቦታል፡፡

ስለ ቀብር ስነስርአቱ የበለጠ መረጃን በዚህ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡- https://www.gov.uk/after-a- death/arrange-the-funeral

**የሞት የምስክር ወረቀት ያስፈልገኛል?**
የሞት ሰርተፍኬት ለውልደትና ሞት ምዝገባ የሚላክ ህጋዊ ሰነድ ሲሆን ይህም የሰውየውን አሟሟትና የሞቱን ምክንያት የሚመዘገብበት ነው፡፡ አስክሬኑ ተለይቶ ወደ ቀብር እንዲሄድ ሲፈቀድ መርማሪው ጊዜአዊ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ የምስክር ወረቀት ሞትን ተከትሎ ለሚመጡ አስተዳደራዊ አካሄዶች ማለትም የባንክ ሂሳብን መዝጋት፣ የጥቅማጥቅም ኤጀንሲዎችን ለማሳወቅ፣ ውርስ ለማግኘት ወዘተ ሊያስፈልጎት ይችላል፡፡

**ከቤትና ሌላ ድጋፍ አንጻር አፋጣኝ ፍላቶች ለሏቸው ቤተሰቦችስ**?
ብዙ ድርጅቶች የእርዳታ እጃቸውን እየዘረጉ እንደሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ሰሜናዊ ኪንግስተን የህግ ማእከል እነዚህን እርዳታዎች እያስተባበረ ሲሆን ስለ ቤት ፍላጎቶች፣ የስደተኛ ሁኔታ፣ የደህንነት ጥቅማጥቅሞች ወይም ስለ ቤተሰቦት አፋጣኝ የገንዘብ ፍላጎቶች የሚፈልጉትን እርዳታ ማግኘቶትን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ **የሰሜናዊ ኪንግስተን የህግ ማእከልን ያግኙ፡-** Unit 15, Baseline Studios, Whitchurch Rd, London W11 4AT. ለመደወል 020 8969 7473 ወይም www.nklc.co.uk ይመልከቱ፡፡

**ቀጥሎ ምን ይሆናል?**
የህዝብ ጥያቄና በሂደት ላይ ያለ የወንጀል ምርመራ ለማጠቃለል የተወሰነ ግዜ ይወስዳል፡፡ እነዚህ ሂደቶች አስጨናቂና ተስፋ አስቆራጭ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን ለድጋፍና ምክር ግዜ እንገኛለን፡፡

---

የባለሙያ ምክርና የህግ ድጋፍ ካስፈለጎት በሚከተለው ያግኙን
መርማሪ፡-
**ስልክ 020 7263 1111**

---